مكانة السنة في الإسلام

የሱና ደረጃ በኢስላም

تأليف:

دكتور صالح بن فوزان بن عبدالله الفوزان

ትርጉም ፡-

ሸይኽ ዩሱፍ አሕመድ

ረመዷን 1441 ሒ.

http://t.me/alateriqilhaq

መቅደም

ውድ አንባቢያን ይህ፡- ዶክተር ሷሊህ ብን ፈውዛን ብን ዓብደላህ አልፈውዛን **"መካነቱ አስሱንናህ ፊል ኢስላም"** (የሱና ደረጃ በኢስላም) በሚል ረዕስ ያስተማሩት አጭር ኮርስ ሲሆን የዓረበኛ ችሎታ ለሌላቸው ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን በሸይኽ ዩሱፍ አህመድ ወደ አማርኛ ተመልሶ በፒዲኤፍ (pdf) ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

በዚህች አጭር ትምህርት፡-

- የሱና ቋንቋዊና ሸሪዓዊ ትርጉም፣
- ሱና በኢስላም ስላለው ደረጃ፣
- በቁርአን ውስጥ የሚገኙ ጥቅል ሐሳቦችን በሱና ካልሆነ መገንዘብ እንደማንችል፣
- ሱናን መቃረን የሚያስከትለው አደጋ፣
- የነብዩ ሶሃቦች رضوان الله عليهم جمعاً ለሱና ያላቸው አክብሮት ትኩረት፣
- ቁርአን እንጂ ሱና አያስፈልግም የሚሉ "ቁርኣንይ" በመባል የሚጠሩ አንጃዎች በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ እየረጩት ላለው ብዥታ ምላሾች እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ተዳሰዋል።

ስለዚህ በጥሞና እናንብበው ሌሎች ወንድሞቻችን እህቶቻችን እንዲያነቡት እናድርግ።

ወቢላሂ አትተውፊቅ

የባህር ዳር አህለሱና መሻይኾች ገፅ

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ለአለማት ጌታ፤ ሶላትና ሰላምታ ደግሞ "ንቁ! እኔ ቁርአንን እና እርሱን የመሰለ ተሰጥቻለሁ።" ብለው በተናገሩት የመጨረሻው ነብይ ሙሐመድ ﷺ ላይ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፡

አላህ سبحانه وتعالى አብሳሪና አስጠንቃቂ ፤ በፈትራ[1] ዘመን የተበላሸውን የጨለማ መንገድ አስተካካይ አብሪና አንጸባራቂ አድርጎ በቅንና በትክክለኛ ሐይማኖት መልክተኛውን ሙሐመድን ﷺ ልኳል። በእርሳቸው አማካኝነት እውራኖች የሚልም ብርሃን ተመልክተዋል ፤ ጠማሞች ወደቅኑ ጎዳና ተመርተዋል። ረሡል ﷺ ግልጽ የሆነን ማድረስ አድርሰዋል ፤ ሌሊቱ ልክ እንደቀን በሆነ ቀጥ ባለ ጎዳና ህዝባቸውን ትተው ሄደዋል።

የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"إني تارك فيكم ما إن تمسكتم به لن تضلوا بعدي كتاب الله وسنتي" الترمذي: ٣٧٨٨

"እኔ በአናንተ ውስጥ አጥብቃችሁ ከያዛችኋቸው ከእኔ በኋላ ፍጹም የማትጠመብትን ትቻለሁ። እርሱም የአላህ ኪታብና የእኔ ሱና ነው።" (ቲርሚዚይ፡ 3788)

የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"فإنه من يعش منكم فسيرى اختلافًا كثيرًا، فعليكم بسنتي، وسنَّة الخلفاءِ الراشدين، عضُّوا عليها بالنَّواجِذِ، وإيَّاكم ومحدثات الأمور؛ فإنَّ كل محدثةٍ بدعةٌ."

أبو داود: ٤٦٠٧، والترمذي: ٢٦٧٦، ابن ماجه: ٤٣، أحمد: ١٧١٤٥، الدارمي: ٩٦

"እንሆ ከእናንተ መካከል የቆየ ሰው በርካታ ልዩነቶችን ይመለከታል። የእኔን ፈለግና የቅን መሪዎችን ፈለግ አደራ ፤ በመንጋጋ ጥርሳችሁ አጥብቃችሁ ያዙ፤ ከነገሮች አዳዲስ ፈጠራዎችን ተጠንቀቁ፤ ማንኛውም አዳዲስ ፈጠራ ቢድዓ ነው፤ ማንኛውም ቢድዓ ደግሞ ጥመት ነው።" (አቡ ዳውድ፡ 4607, ቲርሚዚይ፡ 2676, ኢብኑ ማጀህ፡ 43, አህመድ፡17145, አድዳሪሚይ፡ 96)

(1). በህዝቦች ላይ በአንዱና በሌላኛው ነብይ መካከል ነብያቶች ሳይላኩ የቀሩበት ጊዜ "ፈትራ" በመባል ይጠራል።

በዚህ አላህ በረካ ባደረገው ስብስባችን - ኢንሻአላህ - የማነሳው ርዕስ "የሱና ደረጃ በኢስላም" የሚል ይሆናል።

"ሱና" የሚለው ቃል "መንገድ" የሚል ቋንቋዊ ትርጉም አለው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَهَلْ يَنظُرُونَ إِلَّا سُنَّتَ الْأَوَّلِينَ﴾ فاطر: ٤٣

"የቀድሞዎቹን ደንብ (መንገድ) እንጅ ይጠባበቃሉን?" *(ፋጢር: 43)*

ከዚህ በፊት ሩሡሎችን በመቃረናቸውና በማስተባበላቸው ምክንያት አላህ ውሳኔ ያሳለፈባቸውን ዓይነት ልማድ (መንገድ) እንጅ ሌላን ይጠባበቃሉን? የአላህ ልማድ (መንገድ) የእርሱንና የሩሡሎችን ጠላቶች በቅጣት መያዝ ነው።

የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

"لتتبعن سنن من كان قبلكم" البخاري: ٣٤٥٦، ومسلم: ٢٦٦٩

"ከአናንተ በፊት የነበሩትን ሰዎች መንገድ በእርግጥ ትከተላላችሁ።" *(ቡኻሪ: 3456, ሙስሊም: 2669)*

ይህ ሐዲስ የሚጠቁመው "ሱና" የሚለው ቃል "መንገድ" የሚል ቋንቋዊ ትርጉም እንዳለው ነው።

"ሱና" ከሙሐዲሶች፣ ከኡሱልዮች እና ከፉቀሃዎች ዘንድ ደግሞ የሚከተለው ሸሪዓዊ ትርጉም አለው፡- ከነብዩ ﷺ በንግግር በተግባር እንዲሁም አይተው ያጸደቁት ማለት ነው። አንዳንድ ዑለሞች የነብዩ ﷺ ባሕሪ ወይም መገለጫ "ሱና" በሚለው ትርጓሜ ውስጥ ይካተታል ይላሉ። ከእነዚህ ነገሮች በአንዱ ከተረጋገጠ የረሡል ﷺ "ሱና" ይባላል።

"ሱና" ከቁርአን ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ በመሆኑ በኢስላም ትልቁን ቦታ ይዟል። የመጀመሪያው የዲናችን መሰረት አላህ በረሡል ﷺ ላይ ያወረደው ቅን የሆነው መመሪያ ቁርአን ነው። ሁለተኛው መሰረት የነብዩ ﷺ ሱና ነው። ከእነዚህ በኋላ የሚመጡ የማስረጃ መሰረቶች ሁሉ ወደቁርአንና ወደሱና (ሐዲስ) ይመለሳሉ። በኢስላም መሰረታዊ ማስረጃዎች እነዚህ ሁለት ታላላቅ መሰረቶች ናቸው። ለዚህ ነው የአላህ መልክተኛ ﷺ ሁለቱን መሰረቶች አጥብቀን እንድንይዝ አደራ ያሉት።

"إني تارك فيكم ما إن تمسكتم به لن تضلوا بعدي كتاب الله وسنتي"

"እኔ በአናንተ ውስጥ አጥብቃችሁ ከያዛችኋቸው ከእኔ በኋላ ፍጹም የማትጠመብትን ትቻለሁ። እርሱም የአላህ ኪታብና የእኔ ሱና ነው።" *(ቲርሚዚይ፡ 3788)*

የነብዩ ﷺ ሱና (ሐዲስ) ከአላህ የሆነ ወህይ ለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ነው።

﴿وَمَا يَنطِقُ عَنِ الْهَوَى ۞ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَى﴾ النجم: ٣—٤

"ከሐብ ወዘድም አይናገርም እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራዕይ እንጅ ኬላ አይደለም።" *(ነጅም፡ 3-4)*

ሱና አላህ ወደረሡል ﷺ ያወረደው ወህይ ነው። ሱና ቁርአንን ያብራራል ይተነትናል ግልጽ ያደርጋል። ሱና ጥቅል የሆነውን ይለያያል ልቅ የሆነውን ማሰሪያ ያበጅለታል ፤ አንዳንድ የሸሪዓ አህካሞችን ይሰርዛል ከቁርአን የሌሉ ህጎችንም ይጨምራል።

ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች የሱና አንገብጋቢነትን በግልጽ እንረዳለን ማለት ነው።

"ሱና" ቁርአንን ግልጽ ያደርጋል። ለዚህ ማስረጃችን የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ነው፡-

﴿وَأَنزَلْنَا إِلَيْكَ الذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ﴾ النحل: ٤٤

"ወደአንተም ከሰዎች ወደእነሱ የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸው አወረድን።" (ነህል፡ 44)

አላህ ቁርአንን አወረደ የማብራራቱን ሀላፊነት ደግሞ ለረሡል ﷺ ሰጠ። "በያን" የሚለው ቃል "ሱና" ማለት ነው።

﴿وَمَا أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلاَّ بِلِسَانِ قَوْمِهِ لِيُبَيِّنَ لَهُمْ﴾ إبراهيم: ٤

"ከመልክተኛ ማንኛውንም ከእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በመገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም።" (ኢብራሂም፡ 4)

ረሡል ﷺ ለዚህ ማህበረሰብ ተልከው የመጡት ሊያብራሩ ነው። ለምሳሌ፡- አላህ በቁርአን ሶላትን በጥቅል አዘዘ እንጅ ፈጅር፣ ዙሁር፣ አስር፣ መግሪብ እና ኢሻ ሶላቶች ስንት ረከዓ እንደሚሰገዱ አልተናገረም።

﴿وَأَقِمِ الصَّلَاةَ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاء وَالْمُنكَرِ﴾ العنكبوت: ٤٥

"ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ ። ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና።" (አንከቡት፡ 45)

﴿وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاء وَيُقِيمُوا الصَّلَاةَ﴾ البينة: ٥

"አላህን ሃይማኖትን ከእርሱ ብቻ አጥሪዎች ቀጥተኞች ሆነው ኪግዙት ሶላትንም አስተካክለው ኪሰግዱ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተከያዩ)" (አል'በይናህ፡ 5)

﴿فَإِن تَابُواْ وَأَقَامُواْ الصَّلاَةَ﴾ التوبة: ٥

"ቢጸጸቱም ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ" *(አት-ተውባህ ፡ 5)*

በዚህ ዙሪያ የወረዱ አንቀጾች በርካታ ናቸው።

አላህ ሶላት እንድንሰግድና የምንሰግድበትን ወቅት በጥቅል ተናገረ እንጅ ሶላት የሚሰገድበትን ወቅትና የረከዓዎችን ብዛት አልተናገረም።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿أَقِمِ الصَّلاَةَ لِدُلُوكِ الشَّمْسِ إِلَى غَسَقِ اللَّيْلِ وَقُرْآنَ الْفَجْرِ إِنَّ قُرْآنَ الْفَجْرِ كَانَ مَشْهُودًا﴾ الإسراء: ٧٨

"ሶላትን ከጸሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ። የጎህንም ሶላት ስገድ። የጎህ ሶላት (መላእክት) የሚጣዱት ነውና።" *(አል 'ኢስራእ፡ 78)*

﴿فَسُبْحَانَ اللَّهِ حِينَ تُمْسُونَ وَحِينَ تُصْبِحُونَ ۞ وَلَهُ الْحَمْدُ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَعَشِيًّا وَحِينَ تُظْهِرُونَ﴾ الروم: ١٧–١٨

"አላህንም በምታመሹ ጊዜ በምታነጉም ጊዜ አጥሩት፤ (ስገዱለት)። ምስጋናም በሰማያትና በምድር ውስጥ ከርሱ ብቻ (የተገባው) ነው።"
(አር-ሩም፡ 17-18)

በእነዚህ የቁርአን አንቀጾች ወቅቶች በጥቅል ተነገሩ እንጅ በዝርዝር ተብራርቶ የምናገኘው በሱና ነው።

የአላህ መልክተኛ ﷺ ሶሃቦችን አሰገዱና የሚከተለውን ተናገሩ፡-

"صلوا كما رأيتموني أصلي" البخاري: ٦٣١

“እኔ ስሰግድ እንደተመለከታችሁኝ አድርጋችሁ ስገዱ።” *(ቡኻሪ፡ 631)*

ረሡል ﷺ ሶላትን በተግባር ሰግደው በማሳየት የረከዓዎችን ብዛት ግልጽ አደረጉ። ረሡል ﷺ እንደሰገዱ አድርገን እንሰግዳለን። ዙሁርን፣ ዓሱርን እና ዒሻን በአገር ቤት እያለን አራት ረከዓዎች በሰፈር (መንገደኞች ስንሆን) ደግሞ ሁለት ረከዓዎች አድርገን እንሰግዳለን። መግሪብን በአገር ቤትም ይሁን በሰፈር ሶስት ረከዓዎችን ሱብሂን በአገር ቤትም ይሁን በሰፈር ሁለት ረከዓዎችን እንሰግዳለን።

ወቅቱን አስመልክቶም ረሡል ﷺ ግልጽ አድርገውታል። ዙህርን፣ ዓሱርን፣ መግሪብን፣ ዒሻን እና ፈጅርን በተደነገገላቸው ወቅት መሰረት መስገዳቸውም በሐዲስ ተረጋግጧል።

መላኢካው ጅብሪል عليه السلام ሶላቶችን በመጀመሪያው ወቅትና በመጨረሻው ወቅት ረሡልን ﷺ አሰግዶ ሲያበቃ እንዲህ አለ፡-

"الصلاة بين هذين الوقتين" أحمد: ١١٢٤٩، وأبو داود: ٣٩٣، والترمذي: ١٤٩

“ሶላት በእነዚህ ሁለት ወቅቶች መካከል ነው።” *(አህመድ፡ 11249, አቡ ዳውድ፡ 393, ቲርሚዚይ፡ 149)*

የሶላትን ግዴታነት ጥቅል በሆነ ሁኔታ በቁርአን ብናውቅም የሶላትን ቁጥር የአሰጋገዱን ሁኔታ እና የሚሰገድበትን ወቅት ግን ግልጽ ያደረጉልን ረሡል ﷺ ናቸው።

---

(1). *“አላህ ሶላትን ግዴታ ሲያደርግ በአገር ቤትም ይሁን በመንገደኛ ላይ ሁለት ሁለት ረካዓዎችን ግዴታ አደረገ, የመንገደኛ ሶላት በዛው (በሁለት ረካዓ) ፀና, በአገር ቤት ደግሞ ተጨመረ”* *(ቡኻሪ፡ 350, ሙስሊም፡ 685)*

ዓብደላህ ብን ዑመር እንዲህ ብለዋል፦ “የአላህን መልእክተኛ ጉዞ ባስቸኮላቸው ግዜ የመግሪብን ሶላት ሲያዘገዩ ተመልክቻለሁ, ከዛም ሶስት ረካዓዎችን ሰግደው ያሰላምቱ ነበር” *(ቡኻሪ፡ 1092)*

ሱናን የሚቃወሙ ኸዋሪጆች ወደ ዑመር ብን ዓብዱልአዚዝ ﵀ በመሄድ “ሱናን ማስረጃ ማድረግ ግዴታ ነው ወይስ አይደለም?” በሚለው ዙሪያ ክርክር አነሱ። ዑመር ብን ዓብዱልዓዚዝ ﵀ “አላህ በቁርአኑ ሶላት እንድንሰግድ አዞናል እንዴት ነው የምንሰግደው? እስኪ የሶላትን አኳኋን የሚናገር ከቁርአን አንድ አንቀጽ አምጡልኝ?” በማለት ኸዋሪጆችን ጠየቀ። መልስ በፍጹም ሊመልሱ አልቻሉም፤ በመጨረሻም ተሸንፈው ተመለሱ።

ሐብታሞች ዘካ እንዲያወጡ አላህ በቁርአኑ በጥቅል ትእዛዝ አስተላለፈ እንጅ ከገንዘብ ምን ያክል ዘካ እንደሚወጣ አላብራራም። የዘካ ዝርዝር ህጎችን የምናገኘው በሱና ብቻ ነው። የአላህ መልክተኛ ﷺ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከአዝመራ፣ ከቤት፣ እንሰሳትና ከሸቀጣ ሸቀጥ ምን ያክል መጠን ማውጣት እንዳለብን በደንብ አብራርተዋል። ለምሳሌ፡- የቤት እንሰሳዎች “ሳኢማ” የሆኑት እንጅ ሌሎች ዘካ አይወጣባቸውም። “ሳኢማ” ማለት መስክ ተሰማርተው ግጦሽ ግጠው የሚገቡ እንሰሳዎች ናቸው። ይህ የታወቀው በቁርአን ሳይሆን በሱና ነው።

ከመሬት ከሚበቅሉ አዝመራዎች ዘካ ምን ያክል እንደሚወጣ ያብራሩት ረሡል ﷺ ናቸው። ያለምንም ልፋት የሚበቅሉ አዝመራዎች ከአስር አንድ ዘካ ይወጣባቸዋል። የአዝመራው ባለቤት ከፍተኛ ወጭ አውጥቶባቸው የሚበቅሉ አዝመራዎች ደግሞ ከአስር የአንድ እጅ አንድ ሁለተኛ ዘካ ይወጣባቸዋል። ከወርቅና ከብር ከአስር የአንድ እጅ አንድ አራተኛ ይወሰዳል። የአርባ ፍየል ወይም በግ ባለሐብት አንድ ፍየል ዘካ ያወጣል። ይህ ሁሉ የተብራራው በቁርአን ሳይሆን በሱና ነው። የግመል ባለቤት እንዲሁ ከአምስት ግመል አንድ ፍየል ፤ ከአስር ግመል ሁለት ፍየል፤ ከአስራ አምስት ግመል ሶስት ፍየል ፤ ከሀያ ግመል አራት ፍየል፤ ከሃያአምስት ግመል ቢንት መኻድ (አንድ አመት ሞልቷት ወደሁለተኛው አመት የተሸጋገረች ግመል) ፤ ከሰላሳ ስድስት ግመል ቢንት ለቡን (ሁለት አመት ሞልቷት ወደሶስተኛው አመት የተሸጋገረች ግመል) ዘካ እንደሚያወጣ የአላህ መልክተኛ ﷺ አብራርተዋል። ገንዘብ አመት ካልሞላው ዘካ እንደማይወጣ ከምድር የሚበቅሉ አዝመራዎች ግን ፍሬው መድረሱ ከታወቀ ዘካ ለማውጣት አመት እንደማይጠበቅ የተብራራው በሱና ነው።

ከመሬት የሚበቅል አዝመራ ፍሬው መብሰሉ ከታወቀ ዘካ ማውጣት ግዴታ እንደሆነ አላህ በሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ ተናግሯል፡-

﴿وَآتُواْ حَقَّهُ يَوْمَ حَصَادِهِ﴾ الأنعام: ١٤١

"በአጨዳውም ጊዜ ተገቢውን (ዘካ) ስጡ።" *(አል'አንዓም: 141)*

አላህ የረመዷን ጾም ግዴታ እንደሆነና ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ማእዘን እንደሆነ በጥቅል ተናግሯል።[1] ነገር ግን የጾምን ዝርዝር ህግጋቶች አልተናገረም። ጾምን የሚያፈርሱ ዝርዝር ነገሮች በሱና እንጅ በቁርአን አናገኛቸውም።

ወደተከበረው የአላህ ቤት ሐጅ ማድረግ እንዳለብን በጥቅል ቁርአን ተናገረ እንጅ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሱና ነው የተብራራው።

﴿وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلاً﴾ آل عمران: ٩٧

"ከአካሀም በሰዎች ላይ ወደርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው።" *(አል'ኢምራን :97)*

ይህ የቁርአን አንቀጽ አቅም ያለው ሰው ሐጅ ግዴታ እንደሆነበት ገለጸ እንጅ ሐጅ የምናደርግበትን ወቅት እና የሐጅን አፈጻጸም ስርዓት አልተናገረም ። ስርዓቱ የተብራራው በሐጂተል ወዳዕ (በመሰናበቻው ሐጅ) ነው። በሐጂተል ወዳዕ አንድ በአንድ የሐጅን ስርዓት ከገለጹ በኋላ የሚከተለውን ጥቅል ንግግር እንደተናገሩ የእርሳቸውን ተግባር በአካል ተገኝቶ የተመለከተው ሶሃባ አስተላልፏል፡-

"**خذوا عني مناسككم**" رواه مسلم: ١٢٩٧، وغيره

"ከእኔ የሐጅን ስርዓት ያዙ።" *(ሙስሊም: 1297 ሌሎችም ዘግበውታል)*

(1). ﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ﴾ البقرة: ١٨٣

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በእናንተ ላይ ተጻፈ (ግዴታ ሆነ)" በቀራህ: 183

የሌባ እጅ እንዲቆረጥ አላህ በጥቅል አሏል።

﴿وَالسَّارِقُ وَالسَّارِقَةُ فَاقْطَعُواْ أَيْدِيَهُمَا﴾

"ሰራቂውንና ሰራቂይቱንም በሰሩት ነገር ከቅጣት ከአላህ የሆነን መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ።" *(ማኢዳህ፡ 38)*

የሌባ እጅ ሲቆረጥ የራሱ የሆነ መስፈርት እና ስርዓት ያለው ሲሆን ይህ መስፈርት በቁርአን አልተወሳም። መስፈርቱን የምናገኘው በነብዩ ﷺ ሱና ነው። አንድ ሰው እጁ ሊቆረጥ ዘንድ የሰረቀው መጠን የዲናር ሩብ ወይም ሶስት ዲርሃም ወይም እርሱን የሚስተካከል መሆን አለበት። እንደዚሁ እጅ መቆረጡን እንጅ የት ቦታ እንደሚቆረጥ በሱና እንጅ በቁርአን አልተነገረም። የሚቆረጠው ከቀኝ እጁ የመዳፉ መለያያ **"ኩዕ"** በመባል በሚታወቀው ቦታ ላይ እንደሆነ በሱና ተብራርቷል።

አላህ ረሡልን ﷺ መታዘዝ እንዳለብን ረሡልን ﷺ የታዘዘ ደግሞ አላህን እንደታዘዘ የሚቆጠር መሆኑን ነግሮናል።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿مَّنْ يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللهَ﴾ النساء: ٨٠

"መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ።" *(ኒሳእ፡ 80)*

ከረሡል ﷺ ለተረጋገጠው ሱና ታዛዥ መሆን እና በዚያ መተግበር ረሡልን ﷺ ከመታዘዝ ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا﴾ الحشر: ٧

"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።" *(ሐሸር፡7)*

በዚህ የቁርአን አንቀጽ ከረሡል ﷺ የመጣውን ማንኛውም ትእዛዝ እንድንይዝ የከለከሉንን ደግሞ በሙሉ እንድንከለከል አላህ መመሪያ አስተላልፏል።

በርካታ የቁርአን አንቀጾች ረሡልን ﷺ መታዘዝ እንዳለብን ይገልጻሉ። አንዳንድ ጊዜ ረሡልን ﷺ መታዘዝ አላህን ከመታዘዝ ጋር ተቆራኝቶ ይመጣል።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ أَطِيعُواْ اللهَ وَأَطِيعُواْ الرَّسُولَ وَأُوْلِي الأَمْرِ مِنكُمْ﴾ النساء: ٥٩

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ። መልክተኛውንና ከእናንተም የለልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ።" *(ኒሳእ፡59)*

﴿قُلْ أَطِيعُواْ اللهَ وَالرَّسُولَ﴾ آل عمران: ٣٢

"አላህን እና መልክተኛውን ታዘዙ።" *(አል'ኢምራን፡32)*

አንዳንድ ጊዜ ረሡልን ﷺ መታዘዝ እንዳለብን የሚያዙ የቁርዓን አንቀጾች ብቻቸውን ይመጣሉ።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿مَّنْ يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللهَ﴾ النساء: ٨٠

"መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ።" *(አን'ኒሳዕ፡80)*

﴿وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ﴾ النور: ٥٦

"ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ። ዘካትንም ስጡ። መልክተኛውንም ታዘዙ። ከእናንተ ኪታዘንላችሁ ይከጀላልና።" *(ኑር፡56)*

﴿وَمَا أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلاَّ لِيُطَاعَ بِإِذْنِ اللهِ﴾ النساء: ٦٤

"ማንንም መልክተኛ በአላህ ፈቃድ ኪታዘዙት እንጅ አልላክንም።"
(አን'ኒሳዕ ፡64)

በጭቅጭቅ ጊዜ ወደአላህ ኪታብ (ቁርአን) እና ወደረሡል ﷺ ሱና (ሐዲስ) መመለስ እንዳለብን አላህ አዟል።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ أَطِيعُواْ اللّهَ وَأَطِيعُواْ الرَّسُولَ وَأُوْلِي الأَمْرِ مِنكُمْ فَإِن تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللّهِ وَالرَّسُولِ إِن كُنتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللّهِ وَالْيَوْمِ الآخِرِ ذَلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلاً ﴾ النساء: ٥٩

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ። መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ። በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ የተከራከራችሁበትን (ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው።" *(ኒሳዕ: 59)*

ወደአላህ መመለስ ማለት ወደአላህ ኪታብ መመለስ ማለት ነው። ወደረሡል ﷺ መመለስ ማለት ደግሞ በህይዎት ካሉ ወደእርሳቸው መመለስ ማለት ሲሆን ከሞቱ በኋላ ከሆነ ግን ወደሱናቸው (ወደሐዲስ) መመለስ ማለት ነው።

ወደአላህ ኪታብና ወደረሡል ﷺ ሱና መመለስ እስከቂያማ ቀን ድረስ ቋሚ የሆነ ሕግ ነው። ከሞቱ በኋላ ወደረሡል ﷺ ሱና መመለስ የሚጠቁመው በኢባዳ ጉዳይም ይሁን በሰው ልጆች ሐቅ መካከል ውዝግብ ቢነሳ የእርሳቸው ሱና ጭቅጭን ለመፍታት ዋና ምንጭ መሆኑን ነው። ውዝግብ ከተነሳ ቁርአንም ይሁን ሱና በእኩል ደረጃ የመፍትሄ አካል ይሆናሉ።

ስለዚህ ሱና ከቁርአን ጋር የሚነጣጠል አይደለም። ሱና ከኢስላማዊ ሸሪዓ መሰረቶች አንዱ መሰረት ነው። በማንኛውም ወቅት ማንኛውም ሙስሊም ከሱና ሊብቃቃ አይችልም።

የረሡልን ﷺ ሱና የሚቃረኑ ሰዎች አላህ ከባድ ዛቻን ዝቶባቸዋል፡-

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ﴾ الحشر: ٧

"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።አላህንም ፍሩ። አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና።" *(ሐሸር፡ 7)*

ይህ የቁርአን አንቀጽ የሚጠቁመው በሚያዙትም ይሁን በሚከለክሉት የረሡልን ﷺ ሱና የተቃረነ ለአላህ ቅጣት የተጋለጠ መሆኑን ነው።

አላህ እንደሚከተለው ተናግሯል፡-

﴿فَإِن لَّمْ يَسْتَجِيبُوا لَكَ فَاعْلَمْ أَنَّمَا يَتَّبِعُونَ أَهْوَاءهُمْ﴾ القصص: ٥٠

"እሺ ባይሉህም ፤ የሚከተሉት ፤ ዝንባሌዎቻቸውን ብቻ መሆኑን እወቅ።" *(ቀሶስ፡ 50)*

"ሁሉም ጀነት ይገባል አምቢ ያለ ሲቀር" በማለት የአላህ መልክተኛ ተናገሩ። *"የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማን ነው (ጀነት ግባ ሲባል) እምቢ የሚል?"* በማለት ሶሃቦች ጠየቁ። **"እኔን የታዘዘ ጀነት ገባ እኔን የነቀፈ ደግሞ በእርግጥ አምቢ አለ።"** *(ቡኻሪ፡ 2655/6851)*

ረሡልን ﷺ እና ሱናቸውን የነቀፈ ጀነት ከመግባት እምቢተኛ የሆነና በእሳት የተዛተበት ሰው ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَلْيَحْذَرِ الَّذِينَ يُخَالِفُونَ عَنْ أَمْرِهِ أَن تُصِيبَهُمْ فِتْنَةٌ أَوْ يُصِيبَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ﴾

النور: ٦٣

"እነዚያም ትእዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ።" (ኑር፡ 63)

ረሡልን ﷺ የተቃረነ በሁለት ከባድ ዛቻዎች ተዝቶበታል።

አንደኛው፡- በልቡ ውስጥ ፈተና ይገጥመዋል። ረሡልን ﷺ በመቃረኑ ከሐቅ ያዘነብላል፤ ከኢማን በኋላ ይክዳል፤ በጥመት ልቡን ያበላሻል ፤ በመጨረሻም ወደ ሐቁ አይመራም። ይህ ከሁለተኛው ቅጣት በጣም የበረታ ነው።

ሁለተኛው፡- አሳማሚ ቅጣት የሚለው ነው። ቅጣቱ አንድም በዱንያ ላይ የረሡልን ﷺ ትዕዛዝ በሚቃረኑ ከሐዲዎች ላይ በመገደል፣ በመታመም ወይም በጥፋት መቀጣታቸው ነው። ሁለተኛው ቅጣት በአኼራ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት ነው።

ሆን ብሎ የረሱልን ትእዛዝ የተቃረነ ከሁለቱ ቅጣቶች አያመልጥም። አንደኛው የልብ ቅጣት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአካል፣ የገንዘብ እና የሞት ቅጣት ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلَا مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ وَمَن يَعْصِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا مُّبِينًا﴾

الأحزاب: ٣٦

"አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ከምእምናንና ከምእምናት ከነገራቸው ከእነርሱ ምርጫ ኪኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።" (አህዛብ፡ 36)

ይህ የቁርአን አንቀጽ የሙእሚኖችን ሁኔታ ግልጽ ያደርጋል። የአላህን እና የረሡልን ﷺ ሁክም (ፍርድ) ካወቀ በኋላ በልቡ ደስተኛ እና የተረጋጋ ሆኖ መቀበል እንጅ ከፈለገ ለመስራት ካልፈለገ ለመተው ምርጫ የሌለው መሆኑን ይገልጻል። ምክንያቱም የአላህና የረሡል ﷺ ትእዛዞች ሁሉም ቅን እና መልካም ናቸው።

ከአላህና ከረሡል ﷺ ምርጫ ውጭ ሌላ ምርጫ አለኝ ካለ እንዲህ አይነቱ ሰው ግልጽ የሆነን መጥመም ጠመመ። ጥመት የቅን ጎዳና ተቃራኒ ነው። ከዚህ ቦታ አላህና ረሡል ﷺ ያዘዙትን ትክክለኛ ጎዳና መቃረን ከባድ መሆኑን ለመግለጽ **"ግልጽ የሆነ ጥመት"** በሚል ቋንቋ ቁርአኑ አስቀምጦታል።

የአላህን እና የረሡልን ﷺ ትእዛዝ መቃረን የሚያመጣው ቅጣት ከባድ መሆኑን በቀኝ እጅህ ብላ ሲባል በግራ እጁ በመብላት ተቃርኖውን የገለጸው ሰው ሐዲስ ግልጽ ያደርገዋል።

ነብዩ ﷺ በቀኝ እጁ እንዲመገብ አዘዙት እርሱ ግን ሱናውን ከመተግበር ኩራቱ ከለከለውና እየቻለ **"አልችልም"** የሚል ምላሽ ሰጣቸው። ነብዩም ﷺ እንዲህ አሉት፡-

"لااستطعت"

"አትቻልም።"

"አትቻልም" በማለት ረሡል ﷺ ረገሙት። እርግማኑ ደርሶ እጁ ልክ እንደእንጨት ደረቀ ፤ ከዚያ በኋላ ምግብ ለመብላት ወደአፉ ከፍ ማድረግ አልቻለም። *(ሙስሊም፡ 2021)*

የረሡልን ﷺ ትዕዛዝ በኩራት አማካኝነት የሚቃረን በዚህ ዱንያዊ ምድር ፈጣን የሆነ ቅጣት እንደሚደርስበት ይህ ሐዲስ ትልቅ ማስረጃ ነው።

ባሳለፍነው ሐዲስ ተቃራኒ ደግሞ ነብዩ ﷺ ከአንድ ሶሃባ እጣት የወርቅ ቀለበት ተመለከቱ። ከዚያም እንዲህ አሉት፡-

"يعمد أحدكم إلى جمرة من نار فيضعها في يده"

"አንዳችሁ ከእጁ ላይ ሊያደርገው ወደአሳት ፍም ያስባል"

ወዲያውኑ ከእጣቱ ላይ አውልቀው ወረወሩበት። እርሳቸው ከዚያ ቦታ አለመኖራቸውን ያረጋገጡ አንዳንድ ሶሃቦች *"ይህን ቀለበት አንሳና ተጠቀምበት።"* አሉት። ይህ ሙዕሚን ሰው፡ *"ወሏሂ ረሡል ﷺ የወረወሩትን አላነሳም"* በማለት ምላሽ ሰጣቸው። *(ሙስሊም፡ 2090)*

ረሡልን ﷺ በመታዘዝ በኩል የሁለቱን ሰዎች ልዩነት አስተውሉ። የመጀመሪያው የረሡልን ﷺ ትዕዛዝ በኩራት ተቃወመ ሁለተኛው ደግሞ ረሡል ﷺ የወረወሩትን ቀለበት በፍጹም አላነሳም አለ። ሁለተኛው ሰው ለረሡል ﷺ ታዛዥነቱን በማንጸባረቅ ለኢማን ታላቅ ምሳሌና ምልክት ሆነ።

የሶሃቦችን ታዛዥነት ማሳያ ሌላም ምሳሌ እናቅርብ። በመጀመሪያው ስደት ወቅት ሙስሊሞች በአላህ ትእዛዝ ወደበይተል መቅዲስ ፊታቸውን አዙረው ይሰግዱ ነበር። ከዚያም ወደተከበረው መካ ፊታቸውን እንዲያዞሩ አላህ አዘዘ።
አላህ የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿فَوَلِّ وَجْهَكَ شَطْرَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ﴾

"ስለዚህ ፊትህን ወደተከበረው መስጊድ (ወደካዕባ) አቅጣጫ አዙር።"
(በቀራህ :144)

ቂብላው ከበይተል መቅዲስ ወደተከበረው ካዕባ ሲቀየር ያለምንም ተቃውሞ ወደካዕባ ዞሩ። ወደበይተል መቅዲስ የዞሩት በአላህ ትዕዛዝ ነበር አሁኑም ወደካዕባ የዞሩት በአላህ ትዕዛዝ ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿قُل لِّلَّهِ الْمَشْرِقُ وَالْمَغْرِبُ يَهْدِي مَن يَشَاء إِلَى صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ﴾ البقرة: ١٤٢

"ምስራቁም ምእራቡም የአላህ ነው፤ የሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል።" በላቸው። *(በቀራህ፡ 142)*

ሶሃቦች በአላህ ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ አላሳዩም። የቂብላው መቀየርን ያላወቁ ሶሃቦች አስር ሶላትን ወደበይተል መቅዲስ ዞረው ይሰግዱ ነበር። በመስገድ ላይ እያሉ አንድ ሶሃባ ቂብላው መቀየሩን ነገራቸው። ያለምንም ተቃውሞ ያለምንም ጥያቄ አቅጣጫቸውን ወደከዕባ አዞሩ። *(ቡኻሪ፡ 4486)*

እነዚያ በልባቸው በሽታ ወይም ንፍቅና ያለባቸውን ሰዎች ባህሪ ግን አላህ በቁርአኑ እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

﴿سَيَقُولُ السُّفَهَاء مِنَ النَّاسِ مَا وَلاَّهُمْ عَن قِبْلَتِهِمُ الَّتِي كَانُواْ عَلَيْهَا﴾ البقرة: ١٤٢

"ከሰዎቹ ቂሎቹ "ከዚያች በርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው ምን አዞራቸው? ይላሉ፤" *(በቀራህ፡ 142)*

እነዚያ በልባቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው በሙእሚኖች ተቃራኒ ለመታዘዝ አይሽቀዳደሙም፤ ይልቁንም ጥያቄና ተቃውሞን ያበዛሉ።

ትክክለኛ ሙስሊሞች ሱና ከኢስላም የማስረጃ መሰረቶች ሁለተኛው መሰረት በመሆኑ ፣ ረሡልን ﷺ በመከተልና በመታዘዝ በረካ የሚገኝ በመሆኑና ሱና ከልብ ወለዳቸው የማይናገሩት ነብይ ንግግር በመሆኑ ያልቁታል ያከብሩታል። ረሡልን ﷺ ልክ በአካል አግኝተው እንደሚሰሙ እና እንደሚታዘዙ ይታዘዛሉ። ትክክለኛው ሰነድ ከደረሳቸውም በሱና ይናገራሉ ወደሱና ይቀሰቅሳሉ።

ሰነዱ የተረጋገጠ ሱና በሚጠቁመው መልክት ወደተግባር ይዞራሉ እንጅ ለጥርጣሬ በር አይከፍቱም። ራሳቸውም ይሁን ሌላው በሱና እንዲተገብር ያደርጋሉ። ዘመኑ ምንም እንኳ ሩቅ ቢሆንም ይህ በመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ውስጥ ሱና በኢስላም የነበረው ቦታ፤ በሱና እንዴት እንደሰሩ፤ በእርሷ እንዴት እንደተብቃቁ ማሳያ ነው።

ረሡል ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

"نضر الله امرءا سمع منا حديثا فبلغه كما سمع فرب مبلغ أوعى من سامع"

أبو داود: ٣٦٦٠، والترمذي: ٢٦٥٧، وابن ماجه: ٢٣٦، أحمد: ٢١٥٩٠

"ከእኛ ሐዲስን ሰምቶ እንደሰማው አድርጎ ያደረሰ አላህ ፊቱን ያብራለት ፤ ከአድማጩ የበለጠ የሚገነዘብና የሚረዳ ስንት የሚደርሰው አለ።" *(አቡ ዳውድ፡ 3660, ቲርሚዚይ፡ 2657, ኢብኑ ማጀህ፡ 236, አህመድ፡ 21590)*

ነብዩ ﷺ እስከቂያማ ድረስ ለሚመጣው ኡማ (ህዝብ) ሱናቸው እንዲደርስ በከፍተኛ ሁኔታ አነሳስተዋል ህዝባቸውን ቀስቅሰዋል።

ረሡል ﷺ በመጨረሻው የመሰናበቻ ሐጅ ላይ ታላቅ የሆነ ኹጥባ ዓረፋ ላይ አድርገዋል፡-

"ከአናንተ የተገኘው ለሌላው ያድርስ ፤ ከአድማጩ የበለጠ የሚገነዘብና የሚረዳ ስንት የሚደርሰው አለ።"

ረሡል ﷺ ከእርሳቸው ሐዲስን ያደመጡ ሶሃቦች ላልተገኙት ወንድሞቻቸው እንዲያስተላልፉ የአደራ መልክት አስተላለፉ። *(ቡኻሪ፡1741)*

በዚህ ምክንያት ሁፋዞች የረሡልን ﷺ ሱና በቃላቸው ሸምድደው ለሌሎች በማስተላለፍ የማይተካ ስራ ሰሩ። ይህ ትኩረታቸው እና ጥረታቸው ካለፉ ማህበረሰቦች አንጻር ሲታይ ላቅ ያለ ድርሻ አለው። ለረሡላቸው ﷺ ፋና ትኩረት የሰጡ በዚህ ምድር ላይ እንደነብዩ ሙሀመድ ﷺ ተከታዮች አንድም የለም። በልባቸው የረሡልን ﷺ ሱና ሸምድደው ይዘዋል ፤ ለሌላው እንዲሸመድድ አድርገዋል ፤ ቀዳሚው ለሚቀጥለው ትውልድ አስተላልፏል፤ የሀፊዙትን በሰነድ ላይ አስፍረዋል።

የአላህ መልክተኛ ለተወሰነ ጊዜ ሐዲስ እንዳይጻፍ የሚከተለውን መመሪያ አስተላልፈው ነበር።

"من كتب عني شيئا فليمحه" مسلم: ٣٠٠٤

"ከእኔ ይዞ የጻፈ ይሰርዘው።" (ሙስሊም: 3004)

ይህን የተናገሩበት ምክንያት ሐዲሱ ከቁርአኑ ጋር እንዳይቀላቀል በመስጋት ወይም ሰዎች ሐዲሱ ከቁርአን ነው ብለው እንዳይጠራጠሩ በማሰብ ነው። ከዚያም አንዳንድ ሶሃቦች እንዲጽፉ ፈቀዱ።

ለምሳሌ ዓብደላህ ብን ዓምር ብን አልዓስ رضي الله عنهما ከሳቸው የሰማውን እንዲጽፍ ከተፈቀደላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። ለዚህ ነው ዓብደላ ብን ዓምር የረሡልን ﷺ ሐዲስ በመዘገብ ቀዳሚ ከሚባሉት ሶሃቦች ተርታ የተሰለፈው። ሙስሊሞች ሐዲሱን ከመጻፍ ይልቅ በቃላቸው መሸምደድን ቅድሚያ ሰጡ። ሱናን በደረታቸው በመያዝ ይማማራሉ ፤ ላልሰማው ያደርሳሉ። ከረሡል ﷺ የተሰማን አንድ ሐዲስ ለመማር ከሂጃዝ ተነስተው ወደግብጽ ይሄዳሉ።

ይህ የሚጠቁመው ሶሃቦቹ ለረሡል ﷺ ሐዲስ ያላቸው ክብር እና ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን ነው።

በዑመር ብን ዓብዱልዓዚዝ ዘመን ሐዲስ በኪታብ መልክ እንዲዘጋጅ ተደረገ። የሐዲስ አጻጻፍ ደረጃውን የጠበቀ ሆነ። ለረሡል ﷺ ሱና ሲሃህ፣ መሳኒድ፣ ጀዋሚእ እና መአጅም የተባሉ ኪታቦች ተዘጋጁ። በአሁኑ ሰዓት የሐዲስ መዛግብት ተጠናቀ በሙስሊሞች እጅ ይገኛል። አላህ - ሱብሃኑሁ ወተዓላ - ዲኑ ከመጨመር እና ከመቀነስ በውሸታሞች ከመምታታት ሁፋዞችን በማዘጋጀት እንዲጠበቅ አደረገ። እከሌ ደካማ ነው እከሌ ሐቀኛ ነው የሚሉ ዘጋቢዎችን አዘጋጀ። ከሌሎች እምነት የማይገኙ ውሸታሙን ከእውነተኛው መለየት የሚያስችል ህግና ደንብ ያቀፉ ታላላቅ ኪታቦች ተዘጋጁ ፤ በዚህም ሱና ተጠበቀ። ሱና ተጠበቀ ማለት ቁርአንም ተጠበቀ ማለት ነው።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ﴾ الحجر: ٩

"እኛ ቁርዓንን እኛው አወረድነው። እኛም ከእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።" *(ሂጅር፡ 9)*

ልክ ቁርአንን አላህ ከመጨመር ከመቀነስ እንደጠበቀው ሁሉ የነብዩንም ﷺ ሱና በዘገባዋ አላህ ጠብቋታል። ምክንያቱም ሱና ቁርአንን ታብራራለች ትተነትናለች ግልጽ ታደርጋለች። ሁለቱን ዋና ምንጮች መጠበቁ ለኢስላማዊ ማህበረሰብ እዝነት ነው።

በዚህ ዘመን ተንኮላቸው ግልጽ ከሆኑትና በረሡል ﷺ ሱና ሰዎችን ጥርጣሬ ውስጥ ለመክተት "ቁርአን ይበቃናል ሱና አያስፈልግም።" ከሚሉ አጥማሚ ቡድኖች ማስጠንቀቅ የግድ ይላል።

"ቁርአን ይበቃናል ሱና አያስፈልገንም" ለሚለው አባባላቸው የሚያቀርቧቸው የቁርአን ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

﴿مَّا فَرَّطْنَا فِي الكِتَابِ مِن شَيْءٍ﴾ الأنعام: ٣٨

"ከመጽሐፉ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም።" *(አንዓም፡ 38)*

﴿وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِّكُلِّ شَيْءٍ﴾ النحل: ٨٩

"መጽሐፉንም ከሁሉም ነገር አብራሪ ሆኖ ባንተ ላይ አወረድነው" *(ነህል፡ 89)*

"ሱና የተወራው በአህድ ወይም በተናጥል ዘገባ እንጂ ልክ እንደቁርአን በሙተዋቲር ወይም ሁሉም በተቀበለው የዘገባ ዓይነት አይደለም" ይላሉ ኸዋሪጆች። "የሐዲስ ዘጋቢዎች ከስህተት እና ከውሸት አይጸዱም ፤ ቁርአን ግን ሁሉም በትክክለኛነቱ የተቀበለው በመሆኑ አስተማማኝ ነው። ስለዚህ ጥርጣሬ ያለበትን ትተን እርግጠኛ የሆንበትን እንይዛለን።" ይላሉ።

እነዚህ ቡድኖች ግን እርኩስ አላማቸውን አንግበው ሸሪዓን ለማበላሸት ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን እያንዳንዱ ሙስሊም ሊገነዘብ ይገባል። “ሸሪዓን ተው ወይም ኢስላምን ተው” በማለት ሳይሆን “በቁርአን ስሩ ከሱና ያብቃቃችኋል።” በማለት አስቀያሚ በሆነና ህዝብን በሚሸውድ ሰይጣናዊ መንገድ ነው ህዝቡን እየቀሰቀሱ የሚገኙት። ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን የሱና አገልግሎት ዜሮ ሆነ ማለት ቁርአንም ዜሮ ይሆናል ማለት ነው። ቁርአንና ሐዲስ ዜሮ ሆኑ ማለት ደግሞ ሸሪዓ በአጠቃላይ ዜሮ ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም ሱና ቁርአንን ያብራራል ይተነትናል ግልጽ ያደርጋል። በመሆኑም ሱና ዜሮ ሆነ ማለት በቁርአን መስራት አንችልም ማለት ነው።

ያለሱና እንዴት ልንሰግድ ነው? እንዴት ልንጾም ነው? እንዴት ዘካ ልናወጣ ነው? እንዴት ሐጅ ልናደርግ ነው? በጋብቻም ይሁን በሌላ ሀራም እና ሀላል የሆኑ ነገሮችን እንዴት ልናውቅ ነው? ይህ በሱና ካልሆነ በሌላ መንገድ መታወቅ አይችልም።

ረሡል ﷺ የኸዋሪጆችን ማንነት ከአስራ አራት ክፍለ ዘመን በፊት ነው በሚከተለው ሐዲስ ግልጽ ያደረጉልን።

"يوشك رجل شبعان متكئ على أريكته يبلغه الحديث عني فيقول : بيننا وبينكم كتاب الله ، ما أحله أحللناه ، وما حرمه حرمناه، قال عليه الصلاة والسلام : ألا وإني أوتيت الكتاب ومثله معه" أبو داود: ٤٦٠٤، وأحمد: ١٧١٧٤

“ከአኔ ሐዲስ በደረሰው ጊዜ በጥጋብ ተወጥሮና በመቀመጫው ተጎልቶ “በአኛና በአናንተ መካከል የአላህ ኪታብ አለ። አርሱ ላላል ያደረገውን ሀላል አናደርጋለን፤ አርሱ ሀራም ያደረገውን ሀራም አናደርጋለን” በማለት ይናገራል። ንቁ አኔ ኪታብ አና አርሱን የመሰለ ተሰጦኛል።” *(አቡ ዳውድ፡ 4604, አህመድ፡ 17174)*

ይህ ሐዲስ ከረሡል ﷺ ተአምሮች መከካል አንዱ ተአምር ነው። እርሳቸው የተናገሩት በእርግጥ ተከሰተ። ነብዩ ﷺ ከእነዚህ ሰዎች አስጠንቅቀዋል። ቁርአንና ሱና እንደተሰጣቸውም ሁለቱም ከአላህ ዘንድ እንደሆኑ አብራርተዋል።

ስለነብዩ ﷺ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا يَنطِقُ عَنِ الْهَوَى ۞ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَى﴾ النجم: ٣—٤

"ከሐብ ወከድም አይናገርም እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ኬላ አይደለም።" *(ነጅም፡ 3-4)*

"ቁርአን በሙተዋቲር ሱና ደግሞ በአሀድ ዘገባ የጸደቀ በመሆኑ ሱና ክፍተት ይገባበታል።" የሚለው የኸዋሪጆች ንግግር ባጢልና ከንቱ የሆነ ማስረጃ ነው። ምክንያቱም ሱና ከዚህ በፊት በሰፊው እንዳብራራነው እንደ ጋዜጠኞች ንግግር ወይም ኹራፋቶች ቂሷ አይደለም። የሐዲስ ዘገባዎች በሙሉ በሐዲስ አጣሪዎች የተዘጋጀ ህግና ስርኣት አላቸው። ከነብዩ ዘመን እስከአሁኑ ሰዓት ድረስ ሐዲስን የሚጠብቁ በቃላቸው የሚሸመድዱ በትክክል የሚያስተላልፉ ሱናን ለመጠበቅ የተዘጋጁ የአላህ ባሮች አሉ። ሱና ዘወትር በአላህ ጥበቃ ስር ነው።

የረሡል ﷺ ሱና ለማንም ዘባራቂ በር የሚከፍት አይደለም። የሐዲስ ጀግናዎች ውሸታሙን ከሐቀኛው የሚለይ የሙስጦለህ ኪታብ አዘጋጅተዋል። የሐዲስ አጣሪዎች የተወሰነ ብዥታ የገባባቸውን ሙደሊሶችን እና በመጨረሻ እድሜያቸው የተቀላቀለባቸውን የሐዲስ ዘጋቢዎች አጋልጠዋል። ሱና በሀጢያተኞች በውሸታሞች እጆች ከመበከል ተጠብቆ እስካሁን ድረስ ወደትውልዱ መተላለፉ በመዛግብት ተጠብቆ መቆየቱ ከአላህ የሆነ ለፍጡራኑ እዝነት እና ችሮታ ነው። ምክንያቱም ለአስመሰዮችና ውሸታሞች ማመሳሰል በር ዘግቷል። ከክፍተትና ከጥርጣሬ ጸድቶ ትክክለኛነቱ ተረጋግጧል።

በረሡል ﷺ ሱና ላይ እንከን በማውጣትና ሱናን በመዝለፍ "በቁርአን እንጅ በሱና መስራት አይበቃም" ያለ ከሀዲ ነው። ምክንያቱም የሸሪዓን ሁለተኛ መሰረት የሆነውን ሱና አስተባበለ። የዚህ ሰው ባህሪ "ረሡልን ﷺ አትታዘዙ ይልቁንም አላህን ብቻ ታዘዙ" በማለት እንደተናገረ አምሳያ ነው። የዚህ ሰው መጨረሻ ወይም ፍጻሜ አላህን አለመታዘዝ ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ﴾ الحشر: ٧

"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።አላህንም ፍሩ። አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና።" *(ሐሸር፡ 7)*

﴿وَمَا يَنطِقُ عَنِ الْهَوَى ۞ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَى﴾ النجم: ٣—٤

"ከልብ ወለድም አይናገርም እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም።" *(ነጅም፡ 3-4)*

በአሁኑ ሰዓት እውቀታቸው ከኪታብ እንጅ ከዓሊም እውቀትን ያልወሰዱ በረሡል ﷺ ሱና ላይ የሚጫወቱ ሌላ ቡድኖችም በእኛ ላይ ብቅ ብለዋል። ምንም አይነት የሙስጦለህ እውቀት ሳይኖራቸው ይህ ዶኢፍ ነው ይህ ሶሂህ ነው ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያው ቡድን ይልቅ ለሱናው በጣም አስጊ ናቸው። የመጀመሪያው ቡድን ማህይምነታቸው ግልጽ ሲሆን እነዚህ ግን እውቀት አለን የዲኑ ተመራማሪ ነን በሚል ሽፋን በሙስሊሙ ውስጥ የተደበቁ ሴረኞች ናቸው።

فلا حول ولا قوة إلا بالله

አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ በመሆኑ ጠቃሚ እውቀትን እና መልካም ስራን ለሁሉም እንዲገጥመው ቅኑን ጎዳና እንዲያሳውቀን ፤ ሀቅን በሀቅነቱ ግልጽ አድርጎ እንዲያሳየንና እንድንከተለው የባጢልን ባጢልነት ግልጽ አድርጎ እንዲያሳየንና እንድንርቀው አላህን እንማጸነዋለን።

وصلى الله وسلم على نبينا محمد.

تأليف:
دكتور صالح بن فوزان بن
عبدالله الفوزان

ትርጉም ፡-
ሸይኽ ዩሱፍ አሕመድ

ረመዷን 1441 ሐ.

ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለው የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq